# እዬተጋለጠ የመጣው የሥርዓቱ ገበናና የሕዝቡ የሞት የሽረት ትግል

ግንቦት 20 ቀን 2015ዓም(28-05-2023)

በዬሳምንቱ እሁድ ቀን በሚተላለፈው ስርጭታችን ከሚደመጡት መካከል የስነጽሑፍ ክፍላችን የሚያቀርበው የትንታኔና ዜና ተኮር ቅንብር ሲሆን በዛሬውም እለት ባሳለፍነው ሳምንት በአገራችን የተከሰቱትን ልዩልዩ ክስተቶች እያነሳ የሚተችባቸው ይሆናል።ከሁሉ መጀመሪያ ግን የዛሬውን የግንቦት 20ን እለት የምናስታውስበትን የታሪክ መዝገብ ገልበጥ አድርገን ለማዬትና ለማስታወስ እንወዳለን።

በአገራችን የዘመናት አቆጣጠር ብዙ የግንቦት ወራቶች አልፈዋል።በዚሁ የግንቦት ወር መጀመሪያ ላይ የግንቦት ልደታ በመባል ቤተሰብና ጎረቤት ተሰብስቦ የሚበላበት የሚጠጣበት ጊዜውን በሳቅና በጨዋታ የሚያሳልፍበት የወሩ መግቢያ እለት ነው።ይህንን አይነቱን በጎ ቀን የያዘው የግንቦት ወር ሌሎችም አስደንጋጭና አደገኛ ድርጊቶችንም ይዞ የመጣ ወር ነው።አንዳንዶቹን ብንጠቅስ፣በአምባገነኑ የደርግ አገዛዝ ላይ የተነሱት ከፍተኛ የወታደር ሹማምንት ያልተሳካ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ አድርገው የከሸፈባቸውና ብዙዎች የተገደሉት በዚሁ የግንቦት ወር 8ኛው ቀን 1981 ዓም ላይ ነበር። ይኸው የግንቦት ወር በ1983 ላይ በኢትዮጵያ ታሪክ የማይረሳ፣አሁን ላለችበት የመከራ ዘመንና ለመበታተኗ አደጋ በር የተከፈተበትን እለት ግንቦት 20ን ይዞ  የመጣበትም ወር ነው።ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የግንቦት ወር በኢትዮጵያውያን ዘንድ የብዙ ክፉቶች የልደት ወር በመሆን ይታወሳል።

ይህ ማለት ከግንቦት በፊት  የነበሩት ወራቶችና ቀኖች ብሩህ ተስፋ የታዬባቸው ሆነው ሳይሆን በተለይ ግንቦት 20 1983 ዓም ከድጡ ወደማጡ ወይም ከሳቱ ወደረመጡ የተገባበት ቀንና ወር በመሆኑ ነው። በወያኔ፣በሻእብያና በኦነግ የሽምቅ ተዋጊ ሃይሎች እንዲሁም በሕዝቡ ትብብር ለ17 ዓመት ሰፍኖ የነበረው የወታደር አምባገነናዊ መንግሥት የተወገደበት እለት መሆኑ በአንድ መልኩ የሚያስደስት ቢሆንም በሌላው መልኩ ከባሰ የጎሳ አገዛዝና ለአገር መበታተን  የተገባበት እለት በመሆኑ በታሪክ ክፉ ቀን ወይም ጥቁር ቀን(Dark Day) ተብሎ ለመመደብ በቅቷል።የወደፊቱ የግንቦት ወር ምን ይዞ እንደሚመጣ ባይታወቅም የተሻለና የበጎ ክስተቶች መታሰቢያ ወር እንዲሆን እንመኛለን።

በዚሁ በግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም ስልጣኑን በጉልበት የተቆጣጠረው የተገንጣዮች ሃይል አልሞ የተነሳው አገሪቱን በጎሳ ሽንሽኖ ለመበታተን በመሆኑ ለዚያ  እንቅፋት ይሆናሉ የሚላቸውን የእምነትና፣ የመከላከያ ተቋማትን እንዲሁም የማህበረሰብ ክፍሎችን ለማፍረስና ለማንበርከክ  ሃ ብሎ የጀመረበት እለት በመሆኑ እለቱ በአሉታዊ ሲታወስ ይኖራል። የጨለማ መንገድ የዘረጋው ቡድን ላለፉት 32 ዓመታት የፈጸመውና እዬፈጸመ ያለው አገር የማፈራረስ ሴራ ከቀን ወደ ቀን፣ከዓመት ወደዓመት እዬጨመረና እያደገ መጣ እንጂ አልቀነሰም።ዛሬ ያገራችን የመኖር ያለመኖር ዕድሏ ከአሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሶ የሞት የሽረት ትግል በመካሄድ ላይ ነው። የጥፋት ዘመቻውን የጀመረው በኦርቶዶክስ ተዋህዶና በምእመኗ፣ በኢትዮጵያዊነቱ በማይደራደረው የአማራው ማህበረሰብ ላይ ነበር። ይህንኑ የማጥፋት ዘመቻውን  መጀመሪያ የሙስሊሙን ማህበረሰብ የእምነት ተቋም ደፍሮ ከተቆጣጠረ በኋላ ለረጅም ጊዜ ሲጎሸማት በቆዬው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ  ካለፈው ጥር 14 ቀን 2015 ዓም ጀምሮ ግልጽ ጦርነት ከፍቶ  የእምነት ተቋማትን ከመፈታተን አልፎ የማናጋትና የማፈራረስ ሴራ አሁን ላይ ካለችበት አደጋ ላይ አድርሷታል።

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በኢትዮጵያ ታሪክና አገራዊ ምስረታ ብሎም በልዑላዊነቷ ላይ የማይናቅ ድርሻ እንዳላት አይካድም።ይህንንም ያወቁት የኢትዮጵያ ጠላቶች አገሪቱን ለመቆጣጠር ወይም ለመበታተን አስበው በሚነሱበት ወቅት በጠላትነት ፈርጀው ለማጥፋት የሚያቅዱት በቤተክርስቲያኗና ለእምነቱ ቀናኢ በሆነው ማህበረሰብ ላይ ነው።

ከሰባት መቶ ዓመት በፊት አውሮፓውያን የራሳቸውን የካቶሎክ እምነት ለማስፈን ሲዘምቱ በመጀመሪያ ዒላማ (ታርጌት) ያደረጉት በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ላይ ነበር።በመሪዎችና በእምነቱ አባቶችና ሊቃውንቱ ያላሰለሰ ትግል የቤተክህነቷንና የአገርን ልዑላዊነት ለማስከበር ችለዋል።የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የእምነት ተቋም ብቻም ሳትሆን የጥበብ፣የታሪክ፣የባህል፣የእውቀት፣የስነምግባር፣የፍትህ፣ የነጻነት፣የአገር ወዳድነት፣የጀግንነት ምንጭና ምሳሌ ነች።በምርምርና እንዲሁም በመድሃኒት ቅመማ፣በኮከብ ቆጠራና (astrology)፣በጊዜ ቅምር፣በሂሳብና ስሌት፣በስነጽሑፍ ፊደል ፈጠራ ግንባር ቀደም ቦታ ይዛለች።አገር በውጭ ጠላት ሲደፈር እንደ አርበኛ ሕዝቡን ቀስቅሳና መርታ ጽላቷን ተሸክማ እዬባረከችና እያበረታታች በጦር ሜዳ የዋለች ተቋም ነች። ይህ በማንም የማይካድ የታሪኳ ገጽ ነው።ይህም በመሆኑ ነው ኢትዮጵያን ለመውረር ወይም ለመበታተን የሚነሱ የውጭና ያገር ውስጥ ጠላቶች አስቀድመው ለማጥፋት ሆ ብለው የሚነሱባት።

ጣልያኖች ኢትዮጵያን በወረሩ ጊዜ የመጀመሪያ የቤት ስራ ያደረጉት የቤተክህነቷን ሰዎች፣አባቶችና ጳጳሳት በስጋዊ ጥቅምና ስልጣን በመደለልና በማግለል ወይም በማስፈራራት እንዲያድሩና ሕዝቡን ለጠላት እንዲገዛ በማሳመን በአገራቸው ላይ ክህደት እንዲፈጽሙ ማድረግ ነበር።በዚህ ሙከራቸው ደካሞቹ ሲያጎበድዱ ጠንካራዎቹ ደግሞ ለእምነታቸው፣ ለቤተክርስቲያኗ ዶግማና ቀኖና፣ለአገራቸው ክብርና፣ለታሪካቸው ሲሉ ለጠላት ማደርን ተጠይፈው የስቃይና የሞት ጽዋ ለመቀበል ቆርጠዋል። ከነዚያም ውስጥ ስማቸው በታሪክ የሚወሳው አቡነ ጴጥሮስ አንዱና ቀዳሚው ናቸው።ኢትዮጵያ በቆራጥ ልጆቿና በእምነት አባቶች ብርታት የወረራትን ጠላት አባራ የነጻነቷ ባለቤት ለመሆን ችላለች። ያንን በሃፍረትና በብስጭት መቀበል ያቃታቸው ወራሪዎች በቀጥታ ጦር አዝምተው ማሸነፍ እንደማይሆንላቸው ሲያውቁ በአገር ውስጥ በባንዳነት ሊሠሩ የሚችሉትን በመመልመል አገር የመበታተን ሴራቸውን በስፋት ቀጠሉበት።በጎሳ ተዋረድ ሕዝቡንና መሬቱን ሸንሽነው አንዱ በሌላው ላይ እንዲነሳና እጁን በእጁ እንዲቆርጥ አደረጉት።በአገሪቱ ተወልደው፣በሕዝብ ግብር ተምረው ለቁምነገር ይበቃሉ የተባሉትን ደካሞች በጎሳ ገመድ ተብትበው ሌላውን እንዲተበትቡ አደረጉ።ዛሬ በዬቦታው የነጻነት ወይም የጎሳ እኩልነት እያሉ ባንዲራ ሰፍተው ኢትዮጵያን ለማፍረስ ጎንበስ ቀና የሚሉት በውጭ ጠላቶች የተመለመሉት አገር በቀል ከሃድያን ናቸው።በትግል ስም እርዳታ እያግበሰበሱ በአገርና በውጭ አገር የተደላደለ ኑሮ እዬኖሩ፣ንብረትና ሃብት እዬሰበሰቡ ድሃውን ሕዝብ ለእልቂት እንዲሰለፍ አድርገውታል።

የጣልያኖችንና የእንግሊዞችን ዱካ ተከትለው የተነሱት አገር በቀል ባንዳዎቹ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ላይ ካራ ስለው በተለያዩ ወቅቶች መነሳታቸው በታሪክ የተመዘገበ ሲሆን ከሃምሳ ዓመት ወዲህም የፈረደበትን ሕዝብ ተገን አድርገው በጎሳና ቋንቋ ህሳቤ ቀስቅሰው በራሱ አገርና በወገኑ ብሎም በእምነቱ ላይ እንዲነሳ ገፋፍተው ለእልቂት እንዲሰለፍ አድርገውታል። የባእዳንን እምነት እንዲከተል የማድረጉ ሙከራ የተሳካላቸው ቢመስልም የኢትዮጵያዊነት ስሜቱን ከልቡ ሙሉ ለሙሉ ሊፍቁት አልቻሉም።ለዚያም ነው የፕሮቴስታንትና የካቶሊክ እምነት ተከታዮች ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና ምእመናን ጎን ቆመው ስርዓቱን በመቃወም የተሰለፉትና ብዙ መከራ ለመቀበል የተገደዱት።

እምነት የግል ነው፣አገርም የጋራ ነው።ዜጋ የፈለገውን እምነት የመከተል መብቱ መጠበቅ አለበት። እምነትና ዜግነት የተለያዩ ነው።አገር የአንድ እምነት ፣የአንድ ባህል፣የአንድ ቋንቋ፣የአንድ ጎሳ መድረክ አይደለም።የዓለም አገራት በሙሉ የአንድ እምነትና ማንነት ነጻ ክልሎች አይደሉም።ሁሉም ተከባብሮ የሚኖርባቸው የጋራ ይዞታዎች ናቸው።ሁሉም እኩል ባለቤትና ባለድርሻ ነው እንጂ ሰጭና ነሽ የለም፤ ሊኖርም አይገባም።ጊዜ በተለወጠ ቁጥር አዲስ እምነቶች፣አስተሳሰቦች፣ባህሎች ፣አብረው ይወለዳሉ።ያ ማለት ግን የሰው ልጅ ተፈጥሮ ይለዋወጣል፣አገርም አገር እዬወለደ ይኖራል ማለት አይደለም። የሚታዬው እውነት አገራት እዬተቀራረቡና አንድ እዬሆኑ፣ ልዩነት እዬጠበበና እየጠፋ የሰው ልጅ ይበልጥ እዬተግባባና እየተቀራረበ ይሄዳል እንጂ ጥንት ወደነበረበት የአውሬነት ደረጃ ሲመለስ አይታይም።ያንን ለማድረግ የሚሞክሩት ከታሪክ ጉዞ ያልተማሩና ከተፈጥሮ ሕግ ጋር የተጣሉ ድውያን ብቻ ናቸው።

በኢትዮጵያ የእምነት ተቋማት ላይ ብዙ ለውጥ ታይቷል። ባለፉት ሃምሳ ዓመቶች የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዩ ቁጥር እዬጨመረ እንጂ እዬቀነሰ አልመጣም።ለዚህ ዋናው ምክንያት የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ዘመኑን የዋጀና ትውልዱን ታሳቢ ያደረገ አስተምሮና በምሳሌነት የሚበቃ ተግባር በመዳከሙ ፣ እንዲሁም በአስተዳደሩ ዙሪያ በሚታዩ ድክመቶች ምክንያት እንደሆነ አይካድም። ቤተእምነቶች የነጋዴ አስተሳሰብ በዋጣቸው አባቶች ቁጥጥር ስር ከዋሉ፣ምእመናኑን ከተኩላ ማዳን ካልቻሉ፣የመልካም ስነምግባር ምሳሌ ካልሆኑ ለቤተክርስቲያኗ መዳከምና ለውድቀታቸው የመጀመሪያ ጉድጓድ ቆፋሪዎች ይሆናሉ።በዚህ ድክመት ላይ የጥፋት ሃይሎች ዱላ ሲጨመርበት የመፈረካከሱን ዕድል ይበልጥ ያሳድገዋል።

በቤተክህነቷ ላይ ሲሸረብ የኖረው ሴራ ከአምስት ወራት በፊት ይፋ ወጥቶ በጥር 14 ቀን 2015 ዓም የኦርቶዶክስ ተዋህዶን መሠረት በሚያናጋ መልኩ ከዶግማና ቀኖናዋ ውጭ በጥቂት የፖለቲካ ካድሬነት ባደሩ ቀሳውስትና ጳጳሳት የጎሳ መፈንቅለ መንበር ሙከራ ተደርጎ የብዙ ምእመናን ህይወት መጥፋቱ፣ ቤተክርስቲያናት መውደማቸውና ንዋዬ ቅዱሳን መዘረፋቸው አይካድም።ያንን ተከትሎ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን የሌላው እምነት ተከታይ፣ካቶሊኩ፣ፕሮቴስታንቱ፣ሙስሊሙ በህብረት ቆሞ ድርጊቱን ተቃውሟል።በተቃውሞው የተደናገጠው የኦነግ የፖለቲካ ክንፉ ወደኋላ በማፈግፈግ ተቃውሞውን ለማብረድ ሕገ ወጥ ቡድኑን በማለሳለስ ሕጋዊ ሲኖዶሱን ሸውዶ ለሌላ ሴራ ተዘጋጅቶ ለጊዜውም ቢሆን የተነሳውን ሕዝባዊ ተቃውሞ ለማብረድ ችሏል።የሕጋዊው ሲኖዶስ የሴራው ጠንሳሽ ከሆነው የኦሮሙማው ቡድን ጋር ባይሞዳሞድና ጣልቃ እንዲገቡበት ባያደርግ ኖሮ የሕዝቡ ቁርጠኝነት አገራችንን ለዘለቄታው ሰላም ያበቃት ነበር የሚለው አስተያዬት እስከአሁን የቁጭት ድምጽ ሆኖ ይሰማል።በሁሉም የሙያ ዘርፍ የተሰለፉት ኢትዮጵያውያን ብቻም ሳይሆኑ የውጭ አገራት የኦርቶዶክስ እምነት ተቋማትና ምእመናን ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ጎን መቆማቸውን በይፋ ገልጸው ነበር። አሁንም ካለፈው ስህተት ተምሮ ለቤተክስርስቲያኗና ለአገራችን ህልውና መቆም ካልተቻለ የአገር አጥፊዎቹ ዓላማ ላለመሳካቱ ዋስትና የለም።እራሳቸውን በአሸዋ ውስጥ እንደቀበረ ጊንጥ ጊዜ ጠብቀው አሁንም በማንሰራራት ሲኖዶሱን ለመከፋፈልና ያሰቡትን ለማድረግ ከሚችሉበት ደረጃ ላይ እንደደረሱ በቅርቡ ታዝበናል።

ሕጋዊ ሲኖዶሱ መንበሩን የፖለቲካው ቡድን እንዲጫወትበትና ጣልቃ እንዲገባበት፣እንዲያዝ እንዲወስንበት ባያደርግ ኖሮ አሁን ከተደረሰበት ደረጃ ላይ ባልተደረሰም ነበር። ሕገወጡ ቡድን በቀኖናው መሰረት ቢጠየቅና ከመንበሩ ቢወገድ ኖሮ አሁን ተግደርዳሪ ሲኖዶስ ለመሆን ባልበቃም ነበር።ሕይወታቸው ለጠፋው፣ለቆሰሉት፣፣ከሥራ ገበታቸው ለታገዱትና በእስርቤት መከራ ለተቀበሉት ፣ለወደመው የቤተክህነት ንብረት ተጠያቂ ሳይኖር አለባብሶ መሄዱ አሁን ላይ የበለጠ ዋጋ በማስከፈል

ላይ ነው። ቤተ ክህነት የፖለቲካ መድረክ ሆናለች።የኦሮሙማው ቡድን ያሻውን የሚያደርግባት የሚሾም የሚሽርባት መድረክ ሆናለች።ቤተክህነት ከጎሳና ቋንቋ የጸዳች ለሁሉም የሰው ልጆች የምትቆም፣ቀሳውስቱና ጳጳሳቱም በችሎታቸው እንጂ በጎሳ ማንነታቸውና በሚናገሩት ቋንቋ የሚመደቡባት በጎሳ ተዋረድ የሚሰገሰጉባት ፓርላማ አይደለችም ነበር።አሁን ግን ያንን የስርዓቱን የጎሳና የቋንቋ አመለካከት እየተከተለች መጥታለች።ይህ አካሄድ ለመጨረሻው ውድቀቷ እንዳያበቃት እንሰጋለን።የኦሮሙማው አሻጥር በሲኖዶሱ ውስጥ ደጋፊዎቹን አብዝቶ መንበሩን የመቆጣጠርና በመጨረሻም የራሱን አገርና የሃይማኖት ተቋማት መፍጠር ነው።በተመሳሳይም ትግራይን ገንጥዬ አገር አደርጋለሁ የሚለው ወያኔ የትግራይን አገረ ስብከት ከሕጋዊው ሲኖዶስ ነጥሎ የራሱን ሲኖዶስና ፓትሪያርክ ለማቋቋም በመንቀሳቀስ ላይ ነው።ይህ በእንዲህ እያለ ከእንቅልፉ ያልነቃ የሚመስለው ሕጋዊ ሲኖዶስ ሰላም በሌለበት አገር ለሰላም ከመታገል ይልቅ የሰላም ኮሚቴ እያለ እራሱን ለጥፋት በማዘጋጀት ላይ ነው።ክፍተት ባለባቸው ቦታዎች ጳጳሳት ይሾሙ በማለትም ስምምነት ላይ ደርሶ ኦነጋውያን በጠዬቁት መሰረት 9 ጳጳሳትን ለማስመረጥ ቀጠሮ ይዟል።ከዚያ በኋላ ነው በድምጽ ብልጫ የኦነጋውያኑ ሕገወጥ ቡድን ሥልጣኑን ተረክቦ የፈለገውን ለማድረግ የሚያስችል እቅድ የተያዘው።

ቤተክህነት በውስጥና በውጭ አገር በራሷ ውስጥ የተጠቀጠቁትን አስመሳይ ሰርጎ ገብ የስርዓቱ ደጋፊ የሆኑትን ጳጳሳት፣ቀሳውስት፣ዲያቆናትና፣ምእመናንን ካላሶገደች ውድቀቷ በራሷ ቤትይጀምራል።ጫና የበዛባቸው አባቶች ከተመደቡበት ሃላፊነት ለመልቀቅ ዳር ዳር እያሉ መሆናቸውን ሰምተናል፣ይህ ግን መከተልና መጓዝ ካለባቸው የቀራኒዎ መንገድ መውጣት እንዳይሆን የአባትነት ሚናቸውን እስከመጨረሻው እንዲወጡት እንማጸናለን።

ሴራው በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ላይ ብቻ ተወስኖ አልቀረም። የኢትዮጵያ ሙስሊም መጅሊሱም በዛው በጎሰኞች በትር እዬተቀጠቀጠ ይገኛል፣የመረጣቸውን ኢማም ተቀምቶ በማያውቃቸውና ባልመረጣቸው ኢማም እንዲመራ ከተደረገ ዓመት አልፎታል።የተቃወሙት በጥይት ይደበደባሉ፣ ይሳደዳሉ፣በእስርቤት ይሰቃያሉ።መስጊዶች ይቃጠላሉ፣ንብረት ይዘረፋል።ለኦሮሙማው ቤተመንግሥት መስሪያ ሲባል ንጹሃን ዜጎች ቤታቸው እዬፈረሰ ሜዳ ላይ ይወድቃሉ።እነዚህን የረዳና ያስጠጋ እስከ15 ሽህ ብር ቅጣትና የ3 ወር እስራት ይጠብቀዋል። ይህንን ግፍ መቀበል የከበደው ሙስሊም ባለፈው አርብ ቀን ኔ በመከረኛው የግንቦት ወር 18ኛ ቀን ለጁምአ ጸሎት በወጣበት እለት ብሶቱን ለመግለጽ በመስጊዱ ግቢ ድምጹን ለማሰማት ሲሞክር በስርዓቱ ቅጥረኞች የተከበረው መስጊድ በር ተሰብሮ በሕዝበ ሙስሊሙ ላይ የአስለቃሽ ጭስና የጥይት ሩምታ በመከፈት ከፍተኛና አሰቃቂ ጉዳት ደርሶባቸዋል። ባልታጠቀው ሰላማዊ ዜጋ ላይ በደረሰው ጥቃት የሞቱት ቁጥራቸው በቅጡ ባይታወቅም እንዳሉና ብዞዎች እንደቆሰሉ የዓይን እማኞች ገልጸዋል። ሙስሊም ወገኖቻችን ፍጹም ሰላማዊ በሆነና የፈጣሪያቸውን ስም እዬጠሩ ብሶታቸውን ለመግለጽ ሲሞክሩ የደረሰባቸውን ጉዳት ሁሉም ሊያወግዘውና ከጎናቸው ሊቆም ይገባል።የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በተመሳሳይ ደረጃ ጥቃት ሲደርስባት ከክርስቲያኑ ወገኑ ጎን ቆሞ መከራ የተካፈለው ሙስሊም ወገናችንን አሁን ለጥቃት ሲጋለጥ ከዳር ቆሞ በዝምታ ማዬት እንደማይገባ በተግባር መግለጽ ከሁሉም አገር ወዳድ ይጠበቃል።ገሎ ማልቀስ ልማዱ የሆነው የኦሮሙማው ቡድን ጥፋቱን በንጹሃኑ ላይ ደፍድፎ ከሞትና ከመቁሰል የተረፉትን በማሳደድ ላይ ነው።ከሁለት መቶ በላይ አፍሶ ያሰረ ሲሆን ገና ብዙ ሽህ ሙስሊሞች ለመታሰር በመሳደድ ላይ ናቸው።

የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ማነህ ባለሳምንት በሚል ተራ ሰልፍ መሆኗን ተገንዝባና ነገ ሊገጥማት የሚችለው ተመሳሳይ አደጋ መኖሩን ተረድታ ከሙስሊም ወገኖቻችን ጋር እንድትቆምና የአሸባሪውንና

የጨፍጫፊውን የኦሮሙማ ቡድን ማውገዝ ብቻም ሳይሆን መታገል ያለባት ጊዜው አሁን ነው እንላለን።

ሥርዓቱ የደረሰበትን  የፖለቲካ ኪሳራ በጉልበት ለማካካስና ሰጥ ለጥ አድርጎ ለመግዛት የቆረጠበት ሰዓት ላይ ደርሷል።የኤኮኖሚውንም መከስከስና የሠራተኛውን ደሞዝ ለመክፈል የገባበትን ችግር ለመወጣት ሠራተኛውን፣ነጋዴውንና  ገንዘብ አለው የተባለውን ሁሉ እያስጨነቀና ከፍተኛ የግብር ተመን እዬጣለበት ይገኛል።የቤትና የንብረት ባለቤት በሆነውም ላይ ከፍተኛ ግብር ለመጣል በመንቀሳቀስ ላይ ነው።የንብረት ማስረጃውንና የቦታና የቤት ካርታውን ይዞ እንዲቀርብ ተገዷል።ይህ እርምጃ ከፍተኛ ግብር ለመሰብሰብ የመንደርደሪያ ምክንያት እንዲሆን ታስቦ የተደረገ እንጂ ለባለንብረቱ መብት ማረጋገጫ ታስቦ አይደለም።በይዞታው መጠን ለመክፈል የማይችለውን ግብር ጥሎ ቦታውን መንጠቅ አንዱ የማፈናቀያ ዘዴ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም።

በሌላውም አቅጣጫ በአማራው ላይ ዘመቻውን አስፋፍቶ ቀጥሎበታል።የወልቃይትና የራያን መሬት ለወያኔ አሳልፎ ለመስጠት፣አገር የመበተኑን ሴራ የሚቃወመውን አማራውን በያቅጣጫው እዬወረረ በመግደልና በመዝረፍ ላይ ጦሩን አሰማርቷል።በወሎ፣በሸዋና በጎጃም ላይ አያሌ ጦሩን አዝምቶ ካዳከመ በኋላ ጎንደርን በተናጠል ከቦ ለማስገበር እቅድ አውጥቶ በመንቀሳቀስ ላይ ነው።ሆኖም ግን ትንታጉ የአማራ ልጅ ፋኖ በቀላሉ እጁን አልሰጠም፤በሚችለው መጠን የጠላትን ወራሪ ሃይል ቅስሙን በመስበር ላይ ነው። በአንዳንዱም የውጊያ ቀጠና የተሰማራው የስርዓቱ ተቀጣሪ ከከፍተኛው አዛዥ ጀምሮ ከግዳጁ እዬኮበለለ ከነመሳሪያው ለፋኖ እጁን የሚሰጠው ቁጥሩ ቀላል አይደለም።በዚህም የሥርዓቱ ተጠሪዎች የሚይዙ የሚጨብጡትን አጥተው እብደታቸው ጨምሯል።አንዱን ሲሉት ሌላው እዬሾለከ ተቸግረዋል።ጭንቀትና ድንጋጤ ባደረባቸው መጠን ተስፋ በመቁረጥ የሚወስዱት የጭካኔ እርምጃ እያደገ መጥቷል።ይህ ደግሞ ለውድቀታቸው ማሳያ ነው።አነጋውያኑ ዙሪያው ገደል ሆኖባቸዋል።  በውጭ አገር ያሰማሩት የገንዘብ ልመና ቡድንም የተሳካለት አይመስልም።የምዕራቡ አገሮችም በኡክሬን ጦርነት ላይ ያለውን ሩስያን የመደገፍና ድምጽ የመንፈጉን አቋም ቀይሮ ለኡክሬን እንዲቆም በማባበልም በማስገደድም ላይ ናቸው።አብይ አህመድ ገንዘብ የሚያገኝና ሥልጣኑንም የሚያድን ከመሰለው እንኳንስ ሩስያን ልጆቹንም ከመሸጥ አይመለስም።

በግልጽ እንደሚታዬው የኦሮሙማውና የወያኔ ቡድን በየፊናው ኢትዮጵያን በታትኖ አገር የመፍጠሩን ጉዞ በቅንጅት ለማካሄዳቸው ሌላ ተጨማሪ  ማስረጃ ማቅረብ አያስፈልግም፤በገሃድ የሚታይ ሃቅ ነው።ጌታቸው ረዳና ሬድዋን ሁሴን በአውሮፓና በአሜሪካ እዬተዘዋወሩ እርዳታና ድጋፍ ለመሰብሰብ በመሯሯጥ ላይ ናቸው።ከሰሞኑ በሆላንድ ዋና ከተማ በአምስተርዳም ከልመና በኋላ ባላቸው የእረፍት ጊዜ ልብሳልብስ፣ጫማና ጌጣጌጥ ለማግበስበስ ሱቅ ለሱቅ ሲዞሩ፣በጀልባ ሲንሸራሸሩ የሚያሳይ የፎቶ ማስረጃ በብዛት ተበትኖ አይተናል።ከቶ የተቸገረ የደሃ አገር መንግሥትን ወክለው ለልመና የወጡ ሰዎች አይመስሉም።መንግሥታትን ከመለመኑ ጎን ለጎንም በውጭ አገር የሚኖረውን ሆዳደርና ጎሰኛ ደጋፊዎቻቸውን ለማነጋገርና በቀጣይ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው መመሪያ ለመስጠት እንደሆነ ብዙ ማስረጃዎች ወጥተዋል።በዋናነት ለሥርዓቱ ያደሩ ጎሰኞችና ሆድ አደሮች በግልና በቡድን ለኦሮሙማው ቡድን የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርጉ በሚያስችለው ላይ እቅድ አውጥተዋል።ከእቅዶቹም ውስጥ በእስፖርትና ባህል እንዲሁም እርዳታ በማሰባሰብ  ዝግጅት ሽፋን ገንዘብ ለማሰባሰብ የወጣው ሲሆን በሆላንድና በጀርመን ሃምቡርግ ከተማ በተከታታይ  የእስፖርት ዝግጅቶቹ እንዲካሄዱ በወጣው መመሪያ የሃምቡርጉ በትናንትናውና በዛሬው እለት በመካሄድ ላይ ሲሆን የአምስተርዳሙ አውሮፓ አቀፍ ዝግጅቱም ከሁለት ወር በኋላ በጁላይ ወር ከ26-28 ድረስ እንደሚካሄድ ታውቋል።

በዓለም ውስጥ የሰብአዊ መብት የጣሱና በወንጀል የሚጠረጠሩ ሰዎች ተይዘው ለፍርድ የሚቀርቡበት የዓለም ወንጀለኞች ፍርድ ቤት በሚገኝባት አገር በሆላንድ እንደነዚህ አይነቶቹ ፣ከአንድ ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ያስፈጁ የጦር ወንጀለኞች የሚዝናኑባት አገር መሆኗ የዓለም ፍርድ ቤቱን ከትዝብት ላይ ከመጣልም አልፎ ፍርድ ቤቱ መዶሻውን የሚያነሳው ለምእራባውያን አናጎበድድም፣ያገራችንን ጥቅምና ልኡላዊነት አናስደፍርም፤አሳልፈን አንሰጥም በሚሉት አገር ወዳዶች ላይ እንደሆነ በግልጽ ያሳያል።

ጌታቸው ረዳ በበኩሉ በአሜሪካ አገር የትግራይ እስፖርትና ባህል ፌስቲቫል በሚል የወያኔ ደጋፊዎች በሚያዘጋጁት ላይ ለመገኘት ወደ አሜሪካ ማምራቱ ተሰምቷል።በአሜሪካ ለብዙ ዓመታት የኢትዮጵያውያን የስፖርትና የባሕል ዝግጅትበሚካሄድበት አገር ውስጥ የትግራይ ብሎ ተገንጥሎ መውጣትና ማዘጋጀት ከአገር ግንጠላው ሂደት ተለይቶ አይታይም።የአነግም እንዲሁ ላለመቀጠሉ ማረጋገጫ የለም። ይህንን በእስፖርት ስም ጸረ ኢትዮጵያ የሆነ እንቅስቃሴ ማውገዝ ብቻም ሳይሆን እንዳይሳካ ማድረግ ከሁሉም አገር ወዳድ ይጠበቃል።በዚህ የሚሳተፉትን ከማህበራዊ ግንኙነት መነጠልና ፊት መንሳት ይገባል።ለስርዓቱ አገልጋይ የሆኑትን ጋዜጠኞች፣ምሁሮችና በዬዘርፉ የሚንቀሳቀሱትን ሆድ አደሮች አደብ እንዲገዙ ማድረግና ማጋለጥ የሁሉም አገር ወዳድ ድርሻ ነው። ሌላው የገንዘብ ማሰባሰቢያው ዘዴ በፈረደበት ሕዝብ ስም እርዳታ በማለት የሚካሄደው ዘረፋ ነው። ለተቸገሩ መርዳቱ ተገቢና ብሔራዊም፣ሰብአዊም ግዴታ ቢሆንም በማን በኩል በእርግጥ ለተቸገሩት ሊደርስ እንደሚችል ማወቁ ብልህነት ነው።የስርዓቱ መጠቀሚያ ላለመሆን ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።ለስርዓቱ እጅ መንሻ በተረጀች ወገኖቻችን ስም የገንዘብ ተፋሰስ ለማድረግ የሚሞክሩትን ላለመተባበር አቋም መውሰድ ትንሹ ተጋድሎ ነው።

ባሳለፍነው ሳምንት ብዙ አስከፊ ሁኔታዎች የታዘብንበት ቢሆንም ጎን ለጎን ይበል የሚያስብል ክስተትም ታይቶበታል።ለብዙ ጊዜ እንዲሆን ብዙሃን ሲጠይቁ ፣እኛም ደጋግመን ስንጠይቅ የነበረው የፋኖዎች ጥምረት የአማራ ሕዝባዊ ግንባር በሚል ስያሜ መቋቋሙ ይፋ ሆኗል።ስለዝርዝሩ ብዙ ለማለት ባንችልም፣ ለግንባሩ ያለንን መልካም ምኞት ለመግለጽ እንሻለን።ሁል ጊዜ እዬተቋቋሙ ከከሰሙት ተራ እንዳይውል ጽሎታችን ነው።ግንባሩ በወታደራዊ ዘርፉ የተቋቋመ መሆኑ አገር ወዳዱን በተለይም አማራውን ከመጥፋት ለመታደግ ታስቦ የሚንቀሳቀስ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ አስገብተን በሌላውም ዘርፍ በፖለቲካውና በቀሩት ዘርፎች የጠራ መመሪያና ዝግጅት የሚያደርግ ክንፍ ይኖራል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።ጠላቶች በፖለቲካ፣በወታደራዊ፣ በኤኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፍ አቅም ያላቸው መሆኑን ተገንዝበ በዚያው ደረጃ ሲሆን በበለጠ መዘጋጀት አስፈላጊ ነው እንላለን።ብዙሃኑን ሊስብና ሊያሰልፍ የሚችል አሰራርና አካሄድም ለግንባሩ ስኬት ወሳኝ መሆኑ እንደማይዘነጋ እንተማመናለን። ግንባሩ በአንድ ግለሰብ ወይም በአንድ የፖለቲካ አመለካከት ዙሪያ ብቻ የሚያጠነጥን ሳይሆን ሁሉም አገር ወዳድ አገር በማዳኑ ትግል የሚሳተፍበት ሆኖ በጋራ አመራር የሚመራ መሆን እንዳለበት እናምናለን።ከሁሉም በላይ ግን መድረኩን ለማስፋትና ሃይሉን ለማብዛት ተብሎ ጠላትና ወንጀል የፈጸመ የሚግበሰበስበት እንዳይሆን መጠንቀቅ ተገቢ ነው።ጠላትና ወዳጅን መለዬት የትግሉን ውጤት ይወስናል።በተለይም ለእርዳታ ሲባል የውጭ ሃይሎች የሚያዙትና ለነሱም ፍላጎት ያደረ ተቀያሪ ጎማ እንዳይሆን፣ ላለመሆን መጠንቀቅ ከሁሉም ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል።የጋራ አመራር ያለው የጋራ ግንባር ለቀጣዩ የሽግግር መንግሥት እርሾ የመሆን ዕድሉ ትልቅ ነውና ግንባሩ ያንን ታሳቢ በማድረግ ተዘጋጅቶ እንዲንቀሳቀስ ለማሳሰብ እንወዳለን።

ግንባሩ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በሙሉ አብረውት እንዲሰለፉ ጥሪ ያደረገ ሲሆን እኛም ጥሪውን እናስተጋባለን።

የሰሞኑ ሌላው አስደሳች ወሬ የአማርኛ ቋንቋ በዓለም አቀፍ መድረኮች እውቅናና ክብር ማግኘቱን የሚያበስረው ነው።በአገር ውስጥ የራሳቸው ቋንቋ የሆነውን አማርኛን ለማጥፋት አነግና ወያኔ አንድ ላይ በመከሩበት ወቅት የሚገርመው ደግሞ አማርኛ ቋንቋን ለማጥፋት የተመካከሩበት ቋንቋ አማርኛ መሆኑን ልብ ይሏል! ቻይና የአማርኛን ቋንቋ በትምህርት ቤቶቿ ለማስተማር መጽሃፎች አዘጋጅታ ወጣቶችን በማስተማር የቅኔና የግጥም ችሎታቸውን በማሳዬት ስታስመሰክር ሩስያ በበኩሏ እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር መወሰኗን ይፋ አድርጋለች። ይህን የሰሙት የአነግና የህወሃት ቡድኖች ምን እንደሚሰማቸው ሲያስቡት ለነሱ ሳይሆን ለሚከተላቸው መንጋ ይብላኝለት ያሰኛል። ይህ የአማርኛ ቋንቋ ከፍታ የኢትዮጵያን ከፍታ የሚያረጋግጥ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። በአፍሪካ ደረጃም አንዱ የሥራ ቋንቋ እንዲሆን የተጀመረው ቅስቀሳ በስፋት ተቀባይነት እያገኘ መጥቷል።ያፍሪካ ልጆች የሚናገሩት የመሆኑ ዕድሉ ከፍተኛ ነው።ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ከነታሪክና እሴቶቻቸው ተከብረው ለመኖራቸው ይህ ምስክርና ማረጋገጫ ነው።

ሌላው በዚሁ ጉደኛ የግንቦት ወር ማጠቃለያ ሳምንት የተሰማው ወሬ የግንቦት ሰባት ውልድ የሆነው የኢዜማ መጠቅለል ነው።ከአህያ ቆዳ የተሰራ ከበሮ ጅብ ሲጮህ ይቀደዳል እንደሚባለው ሕዝባዊ ትግሉ እያደገ ሲመጣ ስርዓቱን ተማምነው ለአብይ አህመድ ሻማ ወጊ የሆኑት ድርጅቶችና ስብስቦች ፣ ግለሰቦችም ጭምር የተጠቀጠቁበትን ድንኳን እዬለቀቁ እግሬ አውጭኝ እንደሚሉ በኢዜማና በኢሳት አባላት ላይ ያዬነው ድራማ ማስረጃ ነው።ሕዝባዊ መሰረት የሌለውና በሃቅ ላይ ያልተመሰረተ ድርጅት መጨረሻው አያምርም፣እንደ እምቧይ ካብ ይናዳል።ከኢዜማ አመራሮች አብዛኛዎቹ የድርጅቱን ገመና ግልጥልጥ አድርገው በሚጥም ቋንቋና አገላለጽ ለሕዝብ አቅርበዋል፤ላለፉት ዓመታት ግንቦት ሰባትን ተከትለው የብርሃኑ ነጋ ጭፍራ በመሆን ለፈጸሙት የፖለቲካ ሴራና የአነግ አጃቢነት ይቅርታ ጠይቀዋል።ከቀረ የዘገዬ ይሻላልና ድርጅቱን መልቀቃቸው፣ማጋለጣቸውና ይቅርታ መጠዬቃቸውን ሳናደንቅ አናልፍም።ይህ ማለት ግን ተመልሰው በሕዝባዊ ትግሉ ውስጥ ገብተው ያንቦጫርቁ ማለት አይደለም፤ቢያንስ ቢያንስ የጥሞና ጊዜ ያስፈልጋቸዋል፣በተግባርም ሊፈተኑ ይገባል።አሁን ብርሃኑ ነጋን አጅቦ እንከፍ እንከፍ የሚለው ጀሌ የለቀቁትን አመራሮች ፈለግ ተከትሎ እራሱን ከጥፋት መሳሪያነት ማዳን ይኖርበታል።በብርሃኑ ነጋ የጎሳ ማንነት ምክንያት በድርጅቱ ውስጥ የገባም የጉራጌ ተወላጅ ከባሰ አዘቅት ውስጥ እንዳይገባና የመጣበትን ማህበረሰብ እንዳያሳፍር በሚታወቅበት ኢትዮጵያዊነት ረድፍ ውስጥ ተሰልፎ የጎሳ ስርዓቱንና አስተሳሰቡን መታገል ይጠበቅበታል። ብርሃኑ ነጋ መቼም ዓይኑን በጨው ያጠበ ሰው ነው፣ ሕዝባዊ ትግሉ እያዬለ ሲመጣ በአጋሮቹ በነነዓምን ዘለቀ፣ አንዳርጋቸው ጽጌና በሌሎቹም በኩል ለመጥለፍ ይሞክር ይሆናል።ዳር ዳር እያሉም ነው።ሙከራው ግን አይሳካለትም።ያለው ዕድል ከአብይ ጋር አብሮ በለውጡ ሰደድ መቃጠል ብቻ ነው። ሌሎቹ ሕገ ጥፋቱን ተቀብለው የብልጽግና አጃቢና ድርጎኛ የሆኑ ድርጅቶች ከዚህ ሊማሩ ይገባል።

ትንተናችንን ለማጠቃለል

በአሁኑ መደረግ የሚገባውን እርምጃ በተመለከተ የአማራ ዓለም አቀፍ ንቅናቄ የሚከተለውን መግለጫና ጥሪ አቅርቧል። አገር አጥፊው ሃይል የሚያጠቃው በብድርና በእርዳታ ከውጭና ከውስጥ በሚያገኘው የገንዘብ ተፋሰስ ስለሆነ ያንን ለማድረቅ በሚያስችለው መንገድ ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ ፣አገር ወዳዱ በመንግሥት ላይ ጫናና እቀባ እንዲጥል ለሚከተሉት ገደቦች ጥሪ አቅርቧል።

1 -ወደ ኢትዮጵያ ለዘመድና ለሌላ ጉዳይ የሚላከውን ገንዘብ በግማሹ መቀነስ

2 -በሸቀጣ ሸቀጥ ሱቆች በኩል ለመንግሥት ግብአት በሚሆነው የምንዛሬ ሂደት ውስጥ አለመሳተፍ

3 -ዶላር በጥቁር በሚልኩት ሱቆችና የንግድ ተቋማት ላይ መረጃ መሰብሰብና ለሕግ ማቅረብ

4 -በአስገዳጅ ሁኔታ የሚላኩ የገንዘብ ዝውውሮች በመንግሥት ባንኮች በኩል እንዳይሆኑ ሌላ አማራጮችን መጠቀም

5 -በኢትዮ/ ቴሌኮም በኩል በሚደረጉ የማባባያና  የመሳቢያ ስልቶች ተጠልፎ በመጠቀም ለአገዛዙ የገቢ ምንጭ ላለመሆን መጠንቀቅ

6 -በተለያዩ ቦታዎች በእርዳታ ስም ለአብይ አህመድ አገዛዝ የወንጀል ተልእኮና የጥፋት ዘመቻ የሚውል ገንዘብ በሚሰበስቡት ላይ እርምጃ መውሰድ፣በዝግጅታቸው ላይ አለመሳተፍ፣አዘጋጆቹን ማጋለጥና  ከማንኛውም ማህበረሰብአዊ ግንኙነት ማግለል

እኛም ከዚህ በላይ የቀረበውን ጥሪ በመቀበል ሌላው አገር ወዳድ ለጥሪው ተግባራዊ መልስ እንዲሰጥ ጥሪ እናደርጋለን።

የተመሰረተው ሕዝባዊ ግንባር ይጠንክር! የጠላቶቻችንን ክንድ ይሰበር!

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘለዓለም ትኑር!!